# ክትባትን ጥሶ የማለፍ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

## ጽሁፍ

*[የመሸጋገሪያ ሙዚቃ]*

*[ትረካ]*

ምናልባት ክትባትን ጥሶ የማለፍ ሁኔታዎች ስለሚለው ቃል ሰምተው ሊሆን እና እነዚህ ምን እና ምን ማለት እንደሆኑ ለማወቅ ፈልገው ሊሆን ይችላል።

ጥሶ የማለፍ ሁኔታዎች የሚፈጠሩት ክትባቱን ሙሉ በሙሉ የተከተቡ ሰዎች አሁንም በCOVID-19 ፖዘቲቭ ሆነው ሲገኙ ነው። ይህ የተለመደ ነው። የትኛውም ክትባት 100% ውጤታማ አይደለም።

ተጨማሪ ሰዎች በተከተቡ ቁጥር ተጨማሪ ጥሶ የማለፍ ጉዳዮች እንሰማለን።

ከአስር ሰዎች ውስጥ ዘጠኙ የተከተቡና አንዱ ያልተከተበ ነው ብለን እንውሰድ። አስሩም ለCOVID-19 ተጋላጭ ከመሆናቸውም በተጨማሪ የሁለቱ የምርመራ ውጤት ፖዘቲቭ ሆኖ ተገኝቷል። አንዱ የተከተበ እና ሌላኛው ያልተከተበው ሰው።

ግማሽ ያክሉ በበሽታው የመያዝ ሁኔታዎች ጥሶ የማለፍ ሁኔታዎች መንስኤዎች ቢሆኑም እንኳ ሌሎች ስምንት የተከተቡ ሰዎች በCOVID-19 የተነሳ ያልታመሙ በመሆኑ ምክንያት ይህ አሳሳች ሊሆን ይችላል።

የቫይረሱ የተለያዩ ዝርያዎች እየተሰራጩ በሄዱ ቁጥር ጥሶ የማለፍ ሁኔታዎች የበለጠ ሊያጋጥሙ ቢችሉም እንኳ ክትባቱን ሙሉ በሙሉ የተከተቡ ሰዎች በጽኑ የመታመም ወይም ሆስፒታል የመግባት እድላቸው በእጅጉ ያነሰ ነው። ስለሆነም ክትባቶቹ ይሰራሉ ማለት ነው!

ይህ ሆስፒታሎች ሁሉንም ሰው ለማስተናገድ የሚችሉ በቂ አልጋዎች ያሏቸው መሆኑን እና ድንገተኛ እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች አልጋዎቹን በፍጥነት ማግኘት የሚችሉ መሆኑን ለማረጋገጥ በእጅጉ አስፈላጊ ነው።

ክትባቱን መውሰድ እራስዎንም ሆነ በዙሪያዎ ያሉ ሰዎችን ከCOVID-19 መከላከልን ለመርዳት ተመራጩ ዘዴ ነው።

ስለ COVID-19 በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚኔሶታ የጤና መምሪያ/ Minnesota Department of Health ድረገጽን በ: www.health.state.mn.us ይጎብኙ።

*[የመሸጋገሪያ ሙዚቃ]*

Minnesota Department of Health
Communications Office
PO Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-4989
health.communications@state.mn.us
www.health.state.mn.us

9/8/21 (Amharic)

*ይህን መረጃ በተለየ አቀራረብ ለማግኘት በሚከተለው ቁጥር ይደውሉ: 651-201-4989።*